# <u>የሁለት ሺው ዐመት ጠመዝማዛ ጉዞ ! የሚቀጥለውስ ምን ዐይነት ጉዞ !!</u>

## <u>የፍራንክፈርት የክሌቱ አመዓት አከባበር !!</u>

በጥቂት በፍራንክፈርትና አካባቢው ኗሪ በሆኑ ውድ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን አነሳሽነት የኢትዮጵያን ሁለት ሺህ ሚሌኒዩም ለማክበር በአውሮፓውያን አቆጣጠር በመስከረም ስምንት 2007 የተዘጋጀው ሰሚናር እጅግ በደመቀ ሁኔታ ተከበረ። ሰሚናሩ እንዳይሳካ ከየቦታው ቅስቀሳ ቢካሄድም ከአሜሪካንና ከስዊድን የመጡ ልኡካንና ተሳታፊዎች በቦታው በመገኘትና ንግግር በማድረግ ለበዓሉ ልዩ ድምቀት በመስጠት መጪው ሺህ ዐመት የድስታ ፣ የፍቅር ፣ ሴት ወንድ ሳይል ፣ በጎሳ ሳንገደብ ፣ በሃይማኖት ጥላ ስር ሳንከለል እጃችንን አንድ ላይ በማጣመር የተከበረችና አዲስ ኢትዮጵያን ለመገንባትና ብልጽግናን የምናይበት እንዲሆን ከልብ የመነጨ ምኞታቸውን ገልጸዋል። በሰሚናሩ ላይ ንግግር ለማድረግም ሆነ ለመሳተፍ በፍራንክፈርትና አካበቢው የሚኖሩ ጀርመኖች በመገኘት ለዝግጅቱ ልዩ ድምቀት ሰጥተውታል።

ሰሚናሩን ለማዘጋጀት የወሰደው ጊዜ አጭር ቢሆንም ፣ አዘጋጂዎች ባሳዩት የተቀላጠፈ ስራና ትብብር የአገራችንን ልዩ ልዩ ታሪካዊና ባህላዊ ስራዎችን ባማረ መልክ በማዘጋጀትና ለሚቀጥለው ትውልድ ሊተላለፍ የሚችል ፣ ተሳታፊዎች ምኞታቸውን የሚገልጹበትና ፊርማቸውን የሚያስቀምጡበት ባሸበረቀ መልክ የተዘጋጀ የዘመን መቁጠሪያ ለበዓሉ አከባበር ለዘለዐለም የማይረሳ ታሪካዊ ቦታ ሰጥቶታል ብሎ መናገር ይቻላል። በዚህ አጋጣሚ ለአዘጋጂዎች በዓሉ ታሪካዊ ቦታን እንዲይዝ ላደረጉት ከፍተኛ ሃላፊነት የተሞላበት የተቀላጠፈና የትብብር ስራ በተሳታፊዎቹ ስም ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ።

በአዘጋጂዎች ጥፋት ሳይሆን ተሳታፊዎች በተባለው ሰዓት ባለመገኘት ሰሚናሩ ዘግየት ብሎ ቢጀምርም በፕሮግራሙ ላይ የተዘረዘረው ዝግጅት በቅደም ተከተል ቀርቦ ሰሚናሩ ስነ ስራዓት ባለው መልክ ሊካሄድ ችሏል። የሰሚናሩ አዘጋጂዎች የመግቢያ ንግግር ካደረጉ በኋላ ስብሰባውን በጸሎት የከፈቱት በፍራንክፈርት ኗሪ የሆኑ ቄስ ልሳነ ወርቅ ውቤ ናቸው። ቄስ ልሳነ ወርቅ በዓሉን እንድናስታውስ ጸሎት ካደረጉ በኋላ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ለምን ከአውሮፓው አቆጣጠር እንደሚለይና ፣ የዘመን መለወጫውም እንደ አውሮፓው በጥር ወር ክረምት በሚያይልበት ወቅት ሳይሆን በመስከረም ወር ፣ አበባዎች በሚፈኩበት ፣ ጸሀይ በምትወጣበትና ህዝባችንም ከጨለማው የክረምት ወራት ተላቆ መጪውን ወራት የብራሀንና የደስታ አድርጎ የሚመለከትበት መሆኑን ይህም ሎጂካዊ እንደሆነ ዘርዘር ያለ ትምህርታዊ ገለጻ ሰጥተዋል። ቄስ ልሳነ ወርቅ የሁለት ሺውን ዘመን መግቢያ አስታከው አገራችን በዓለም ታሪክ ውስጥ ያላትን ልዩ ታሪካዊ ቦታ አጥብቀው በማንሳት ፣ ይህ በዓል የክርስቲያኑ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያውያን በዓል እንደሆነ ፣ ከሃይማኖትና ከጎሳ ልዩነት ባሻገር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይህችን አገር አሁን ካለችበት አዘቀት አውጥቶ በዓለም ዕውነተኛውን ታሪካዊ ቦታ እንድትይዝ ታሪካዊና የሞራል ሃላፊነት እንዳለበት ጥሪ አድርገዋል። ከኝህ አዋቂና ብልህ አስተዋይ ቄስ የተላለፈው ትምህርታዊ መልዕክት በሁሉም ጆሮ የገባ ሲሆን ፣ ጊዜው የሚጠይቀው ዘመናዊና የስልጣኔ መልዕክት እንደሆነ መገንዘቡ ከባድ አይሆንም።

በአዘጋጂዎቹ የተዘጋጀው ሰሚናር ትምህርታዊ እንዲሆን የታሰበ እንደመሆኑ መጠን ባለፉት ሁለት ሺህ ዐመታት አገራችን የተጓዘችበትን ጠመዝማዛ ጎዳና ወጣቱ ትውልድና የጀርመኑ ተጋባዥ እንዲረዳው በልዩ ልዩ አርእስቶች ላይ ንግግር እንዲያደርጉ የተጋበዙት ምሁራን ፣ የሴቶችና የወጣቶች እንዲሁም የድርጅት ተወካዮች ትምህርታዊ አዘል ንግግራቸውን በኮምፒዩተርም ሆነ በቃል በተሰጣቸው አጭር ጊዜ ውስጥ ግሩምና በሳል ንግግሮች አድርገዋል።

ከቄስ ልሳነ ወርቅ ቀጥሎ ስለ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ንግግር እንዲያደርግ ከተጋበዙት ውስጥ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ሲሆን ፣ አቅራቢው አገራችን ባለፉት ሁለት ሺህ ዐመታት የተጓዘችበትን ጠመዝማዛ ጎዳና ከሞላ ጎደል ጠቀስ ጠቀስ እያለ በግራፍ መልክ በተደገፈ ሰዕል አቅርቧል። በአቅራቢው ዕምነት አንድ አገር የተጓዘችብትን የሁለት ሺህ ዐመት የኢኮኖሚ ዕድገት በሰፊው ማሳየት እንደማይቻል ፣ ከጊዜም ሆነ ከማስረጃዎች እጥረት የተነሳ በተወሰኑ ታሪካዊ ሂደቶችና ክንዋኔዎች ላይ ብቻ ማትኮር እንደሚቻል ለቤቱ አሳስቧል። ከዚህም መሰረተ-ሀሳብ በመነሳት ኢትዮጵያ እንደ ህብረ-ብሄር እንድትዋቀርና የመጀመሪያውም መልክ ያለው በመንግሰት ደረጃ የተደራጀ የስራ ክፍፍልና ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከሁለተኛው ምዕተ-ዐመት ጀምሮ እንደሆነና ፣ ይህም ዘመን

በእርግጥ ታሪክ መስራት የተጀመረበትና በተወሰኑ አካባቢዎች የሚኖር ህዝብ አስተሳሰቡን ሰብሰብ አድርጎ ወደ አንድ አማካይ ንጉሳዊ አገዛዝ እንዲመለከት የተደረገበት ጊዜ እንደሆነ መመልከቱ አስፈላጊ መሆኑን አመክልቷል። በዚህም መሰረት ፣ ቀደም ብለው የተካሄዱት ታሪካዊ ክንውኖች እንዳሉ ሆነው የአክሱም አገዛዝ ከተጠነሰሰበትና ቀስ በቀስ እያለ አድጎና ዳብሮ ግዛቱን እያስፋፋ ሲሄድ ሰፊ የኢኮኖሚ መሰረት እንደሚያስፈልገው በመገንዘብ የሩቅ ንግድና ከግብርና የሚገኝ ግብር ለአገዛዙ መንቀሳቀሺያ መሳሪያ ሆነው እንዳገለገሉት ጠቅሷል። በጊዜው ከመዳብና ከነሀስ ገንዘብ ቢታተምም ፣ በገንዘብ ላይ የሚመካ ኢኮኖሚ ሊዳብር እንዳልቻለ ፣ የአገዛዙም አትኩሮ ይበልጥ በውጭ ንግድ ላይና ግዛትን በማስፋፋት ላይ በመወሰኑ ወደ ውስጥ በቂ ማቴሪያላዊ መሰረቶችን ለመጣልና የስራ ክፍፍሉ እንዲዳብር ሊያደርግ አልቻልም። በዚህም ምክንያትና ከተለያዩ አቅጣጨዎች የተሰነዘሩበትን ጥቃት ለመቋቋም ባለመቻሉ በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ላይ ዮዲት በምትባለው የአገው ሴት ድምጥማጡ ሊጠፋ ችሏል። የዮዲትም አነሳስ ከቂም በቀል ጋር የተያያዘ በመሆኑ አርባ ዐመት ያህል ከሰባት መቶ ዐመት በላይ የተገነባውንና የዳበረውን ስልጣኔና መጻህፍት እንዲቃጠልና ድምጥማጡ እንዲጠፋ አድርጋለች። የአክሱም ስልጣኔ ከተደመሰሰ በኋላ የዛግዌ አገዛዝ እስከተነሳበት ጊዜ ድረስና እስከ አስራአንደኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ታሪክ የጨለማ ዘመን ነበር ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።

የዛግዌ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሬናሳንስ የተጀመረበት ዘመን ሲሆን ፣ ይህ እንቅስቃሴ በላሊበላ ታሪካዊ ህንፃ የሚገለጽ እንደነበር ታሪክ ያረጋግጣል። የዛግዌ አገዛዝ ዘመን ይበልጥ የዕደ-ጥብ እንቅስቃሴ የታየበት ዘመን ሲሆን ፣ በሰለሞን ዲይናስቲ እስተተካበት ጊዜ ድረስ ብዙም አልገፋም። በአቅራቢው ዕምነት በኢትዮጵያ ወስጥ የፊዩዳሉ ኢኮኖሚ ከአስራሶስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተመሰረተ ሲሆን ፣ ይህ ስርዓት የኢትዮጵያን የወደፊቱን ዕድል ሊወስን ችሏል።ርስት ፣ ጉልት የተባሉት ስርዓት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እየዳበሩ የመጡ ሲሆን ፣ የስራ ክፍፍል ሊዳብር ያልቻለበት ፣ በሰርዓቱ ግትርነት ከእርሻ ሙያ በስተቀር ንግድና የዕደ-ጥበብ ሙያዎች እንደ አፀያፊ የሚቆጠሩበት ፣ በዚህም ምክንያት በጋብቻም ሆነ በሌላ መልክ ህዝባዊ እንቅስቃሴ(social mobility)እንዳይኖር የታገደበትና ህዝባዊ መተሳሰር ኑሮ ኢኮኖሚው በጸና መሰረት ላይ እንዳይገነባ የታገደበት ዘመን ነው ብሎ መናገር እንደሚቻል አስታወቋል። ስለሆነም ኢኮኖሚው በገንዘብ እንቅስቃሴ ሊገለጽ ያልቻለበትና በአማዛኙ የእቃ በእቃ ልውውጥ ያየለበትና ኢኮኖሚውም በዚህ እንዲወስን የተገደደበት ዘመን ነበር። በዚህም ምክንያት ከተማዎች ሊያድጉ አልቻሉም። ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየተዘዋወሩ ባህልን ሊያዳብሩና ችሎታቸውን ሊያረጋግጡ አልቻሉም። ይህ ዐይነቱ ፊዩዳላዊ አገዛዝ ከስድስት መቶ ዐመት በላይ ሲቆይ ፣ የዘመናዊቱ ኢትዮጵያ ታሪክ የተጣለው በአፄ ዮሃንስ ዘመን ፣ ይበልጥ ደግሞ በአፄ ቴዎድሮስ አገዛዝ ዘመን እንደ ነበር ይታወቃል። አፄ ቴዎድሮስ ሳይማሩ የተገለጸላቸው ምሁር ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያን ታላቅነት የሚመኙና የመጀመሪያውን የስራ ባህል ያስተማሩ ፣ ራሳቸውም መንገድ በመስራት ለስራና ለአገራቸው ዕድገትና ክብር ያላቸውን ፍቅር ያረጋገጡበት ነው።

ስለዘመናዊቱ ኢትዮጵያ ሲነሳ በከፍተኛ ደረጃ መታወስ ያለባቸው አፄ ምኒልክ ናቸው። ካለትልቅ አገር ሰፋ ያለ ኢኮኖሚ መገንባት እንደማይቻል የተረዱ የዘመናዊቱ ኢትዮጵያ አባት ናቸው። የባቡር ሀዲድ ያስገቡ ፣ ቴሌግራፍ እንዲገባ ያደረጉ ፣ የመጀመሪያው ባንክ እንዲቋቋምና ሰፊ የትምህርት መስክ እንዲዘረጋና የተሰበጣጠረው ህዝብ አመለካከቱን ወደ አንድ ማዕከላዊ አገዛዝ በማድረግ ልዩ አገራዊ ስሜት እንዲዳብር ያደረጉ ታላቅ ንጉስ ናቸው። በተጨማሪም ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ እንድትገባና እንድትካፈል ጥንስሱ የተጣለው በአፄ ምኒልክ ዘመን ነው። ይሁንና በወስጥ የፊዩዳል ሽኩቻና የውጭ ሃይሎች ተጽዕኖና አሻጥር ኢኮኖሚው ሰፊ መሰረት ሊይዝ አልቻለም። ህልማቸው ሙሉ በሙሉ ዕውን ሊሆን አልቻለም። የወደፊቱ ኢትዮጵያ ዕድል ከዚያ በኋላ በተነሱት ነገስታት ላይ የተጣለ ሲሆን ፣ የሶስተኛው ዙር ዘመናዊት ኢትዮጵያ አባት አፄ ኃይለስላሴ ናቸው። ከዚያ ቀደም ብሎ ግን ጣሊያን ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር ብሎ የፍጆታ ማምረቻ ኢንዱስትሪ በየቦታው እንደተከለና ከአገዛዙ መዳከም ጋር ፊዩዳሊዝምን እንዳሰወገደ ይታወቃል። ከጣሊያን መባረር በኋላ ኢትዮጵያ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ትገባለች። የአገዛዙን ድክመት ተገንዝባ እንግሊዝ ጣሊያን የተከለውን ኢንዱስትሪና የመንገድና የመመለለሻ መገናኛዎች እየገነጣጠለች ወደ ህንድና ወደ ሌሎች አገሮች ተውስዳለች። በተጨማሪም ህዝቡም የጠላት ንብረት ነው እያለ የተቀረውን መሳሪያ ያወድማል። በሌላ ወገን ደግሞ አፄ ኃይለስላሴ ጣሊያን የደመሰሰውን የፊዩዳሉን ስርዓት እንደገና መልሰው ይተክላሉ። ከፖለቲካ-ኢኮኖሚክስ ህግ አንፃር ይህ ርምጃ የኋሊት ጎዞ ነበር ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። ሆኖም አፄው ዘመናዊ ነክ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ቢያካሄዱም አንድ ወጥ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ማዳበር አልቻሉም። በዓለም የስራ ክፍፍል ውስጥ ገብታ እዚያው በዚያው እንድትንደፋደፍ

የተፈረደባት ኢትዮጵያ ኅዘዋ የኤሊ ጉዞ ሆነ። ዕድገቷና ዕድሏ በህዝቦቿ የሚወሰን መሆኑ ቀርቶ በውጭ ኃይሎች የሚደነገግ ሆነ። ወደ ድህነት እንድትገፈተር በሩ ተከፈተ። አፄው ባለማወቅ የአገራችንን ዕድልና የወጣቱን የወደፊት ዕጣ ጠመዝማዛ አድርገው ሄዱ። አቅራቢው በስታትስቲክስ እንዳመለከተው በአፄው ዘመን የተተከሉት ኢንዱስትሪዎች በሙሉ ውስጠ-ኃይላቸው ደካማና የውስጥ ገበያን ለማዳበር የሚችሉ እንዳልነበር ነው።በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነው የየካቲቱ አብዮት የፈነዳው።

አብዮቱ የታሪክ ግዴታ የሆነውን ያህል ፣ ስር ነቀል ከመሆኑ የተነሳ የፖለቲካ ኢኮኖሚክስን ህግ የሚፃረር ነበር።በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተወሰዱት እርምጃዎች ብዙ ኃይልን አስበረገገ። ከሃምሳኛው ዓ.ም ጀምሮ ቀስ በቀስ እያለ እያደገ የመጣውን ከበርቴያዊና የንዑስ ህብረተ-ሰብ ክፍል እንዲመታ ሆነ። በዚህም ብዙ የማቴሪያልና የሰው ጉልበት ባከነ። በሌላ በኩል ደግሞ ደርግ የወሰደው ኢኮኖሚያዊ እርምጃ በይዘቱ ከድሮ የተለየ ባላመሆኑ የመረቃ ኢኮኖሚ ዕድገት ሊታይ አልቻለም። አቅራቢው በግራፍ እንዳሳየው ዕድገቱ ውጣ ውረድ የበዛበት ሲሆን ፣ የኋላ ኋላ በሰሜን ኮሪያ የተደገፈ ሙሉ በሙሉ የብረታብረትና የማሽን ፋብሪካ በደብረብርሃን ፣ ጋፋት በመባል የሚታወቀው ይቋቋማል። ይህ በቢሮክራሲው የውስጥ ለውስጥ አሻጥር ለአሜሪካኖች ምስጢሩ የባከነው በኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ሙሉ በሙሉ እንዱፈራርስ ይደረጋል። እነ ብልሁ አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ እንደዚህ ዐይነት ኢንዱስትሪ አያስፈልጋትም ፣ ማንኪያና ድስት እንሰራበታለን እያሉ እያፌዙ አፈራረሱት። የኢትዮጵያ ልጆች በኢትዮጵያ ላይ ተንኮል ሲሰሩ !! ሰማያዊ ፈረስ የተባለውን ፊልም መመልከቱ ግሩም ትምህርትን ይሰጠናል።

ከአስራ አምሰት ዐመት ጀምሮ አገራችን የምትከተለው የተቀዋም ኢኮኖሚ ፖሊሲ በመባል የሚታወቀው የእነ አቶ መለስ የገበያ ኢኮኖሚ ነው። የዚህ ፖሊሲ ውጤት ዛሬ አገራችን ያለችበትን ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ጸሀፊው በአሀዝና በግራፍ እንዳሳየው ፣ በደሀና በሀብታም መሀከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መጥቷል። አገሪቱ ከአቅሟ በላይ ብዙ የውጭ ዕቃ ታስመጣለች። በዚህም ምክንያት የውጭው ንግድ በከፍተኛ ደረጃ ተናግቷል። ዕዳው ተቆልሏል። ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ስለሚካሄዱ በአገሪቱ ውስጥ ከፍኛ መዛባት ተፈጥሯል። በአጭሩ ከኢኮኖሚ ዕድገት አኳያ የአገራችን ሁኔታ የሚያዝናና አይደለም። የወደፊቱ ጉዞአችን አስቸጋሪና ጠመዝማዛ ነው ማለት ነው።

የሚቀጥለው ተናጋሪ የጾቸ ቬለ ጋዜጠኛና የታሪክ ተመራማሪ የሆኑት አቶ ክፍሌ የኋላ ናቸው። አቶ ክፍሌ ግሩም በሆነ አቀራረባቸው የአከሱምን ታሪክ የስልጣኔ ትርጉም እንድንረዳ አድርገዋል። በምርምራቸውና በጥናታቸው መሰረት ፣የአክሱም ስልጣኔ አንድ ወጥ ብቻ አልነበረም። ግሩም ግሩም የሆነ የህንጻ አሰራር ቴክኒክ የዳበረበት ፣ የሙዚቃና የሌትሬቸር መሰረቶች የተጣለበትና ኢትዮጵያ ትክክለኛውን የስለጣኔ ፈለግ እንድትይዝ የተደረገችበት ነው። በመርማሪው አቀራረብ ፣ ኢትዮጵያ የስልጣኔ ባለቤት ብቻ አልነበረችም። ከፔርሺያውና ከሮም አገዛዝ ቀጥሎ ሌላዋ ኃያል መንግስትም እንደነበረችና ግዛቷም እስከ ዛሬይቱ የመን ድረስ እንደዘለቀ አስተምረውናል። አቶ ክፍሌ ለአክሱም ስልጣኔ ብቻ ሳይሆን ለዛግዌ አገዛዝ ያላቸው አድናቆት ከፍተኛ ብቻ ሳይሆን ፣ የዛግዌ አገዛዝ በሁለት መቶ አርባ ዐመት ዕድሜው በታሪክ ውስጥ ትዝታን ጥሎ የሄደ ከፍተኛ ስራ እንደሰራና አገዛዙም ለዕደ-ጥበብ ስራ መስፋፋት ያለውጉግትና ማበረታት የቱን ያህል እንደነበር አቅርበዋል።አቶ ክፍሌ የኢትዮጵያን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የግዕዝን ቋንቋ ጠለቅ ብለው ስለሚያውቁ ስለ ዕድገት ያላቸው አመለካከት ሰፋ ያለው ነው።

ቀጥሎ ንግግር ያደረጉት የፖለቲካል ሳይንስና የታሪክ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ግደይ ናይቸው። ዶክተር ግደይ አሰፋ የትግሬ ተወላጅ ሲሆኑ የዛሬውን አገዛዝ አጥብቀው የሚቃወሙና ስለ ህብረተሰብና ስለ ዲሞክራሲ ያላቸው አስተያየት ሰፋ ያለ ነው። ፍልስፍናን ባዘለ ሰፊና ትምህርታዊ ንግግራቸው ስለዲሞክራሲ ምንነትና አንድ ህዝብ በዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ውስጥ መኖር ሳለለበት ተፈጥሮአዊ ህግ ዘርዘር አድርገው አቅርበዋል። ዲሞክራሲ በአጠቃላይ መልኩ መታየት ያለበት ብቻ ሳይሆን በግለሰቦች ነፃነት የሚገለጽ ፣ የአንድ አገር ዕድገትና አቅጠጫ በዲሞክራሲ መኖራና አለመኖር የሚወሰን ነው። ዲሞክራሲዊ ሰርዓት በሌለበት አገር ውስጥ ሽፍጠኝነትና አለመተማመን እንደባህል ይወሰዳል። ይህን ሁኔታ አስታከው ጥቂት ኃይሎች አምባገነን አገዛዛቸውን በማስፈን የሰውን የመፍጠር ችሎታ ያፍናሉ። ህዝብን ለድንቁርና ይዳርጋሉ። ስለዚህም ይላሉ ዶክተር ግደይ ፣ ዴሞክራሲ በአንድ አገዛዝ ተለክቶ የሚወስን ሳይሆን እንደ አየር ለሰው ልጅ የሚያስፈልገው ፣ ሃሳቡን በነጻ የሚያንሸራሽርበት ፣ ይህ ተግባራዊ እስካልሆነ ድረስ ማንኛውም ግለሰብ ነጻነት ሊሰማው አይገባም ይላሉ። ዶክተር ግደይ የብሄረ-ሰቦች መከበር አስፈላጊ የሆነውን ያህል ፣ የአንድ ብሄረ-ሰብ አገዛዝ ጥፋትን እንጂን ልማትን

እንደማያመጣ ይናገራሉ። በመሆኑም የዛሬው አገዛዝ በአማዛኝ ጎኑ ከትግሬ ብሄረ-ሰብ በመውጣቱ ጠቅላላውን የትግሬን ህዝብ ጥቅም እንዳላስጠበቀ ያረጋግጣሉ። ስለዚህም በዚህ ላይ የሚደረገው ያማያስፈልግ ዘመቻ ቆሞ ዲሞክራሲ የሰፈነባት ፣ ህዝቦቿ እጃቸውን በአንድነት አንስተው የሚገነቧትና ከትውልድ ትውልድ የምትተላለፍ አዲስ አገር መገንባት የጊዜው አንገብጋቤ ጥያቄ መሆኑን ያመለክታሉ። በተጨማሪም የዛሬው አገዛዝ ከስልጣኑ ሊወገድ የሚችለው በተባበረና የግለሰብን ነጻነት ባካተተ ዲሞክራሲዊ ትግል መሆኑን እያመለከቱ ፣የአገዛዙ ስልጣን ላይ መቆየት ደግሞ የአገራችንን ጥፋት እንደሚያፋጥነው ያመለክታሉ።

ከዚህ ቀጥሎ የተናገሩት የጀርመኑ ተወላጅ ሚስተር ፍሪዚከ የሚባሉት የአፍሪቃ ተመራማሪና የረጅም ጊዜ የሺለር ኢንስቲቱት ባልደረባና ቋሚ ሰራተኛ የነበሩ ናቸው። ሚሰተር ፍሪዚከ ከሰላሳ ዐመት በላይ ስለ አፍረቃ ጽፈዋል። የአፍሪቃንና የዓለምን ፖለቲካ ጠንቅቀው የሚያውቁ በሰፊው የሚያሰቡ ናቸው። ንግግራቸውም ስትራቴጂያዊና በሰፊው እንደንመለከት የሚጋብዘን ፣ የዓለም ፖለቲካ ውጥንቅጥ የተሞላበት መሆኑን የሚያሳይ ነው። አቶ ፍሬዚከ የኢትዮጵያን ልዩና ታሪካዊ ቦታ ካተቱ በኋላ ፣ በአጠቃላይ ግን ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፖለቲካ ከዳፋርና ከኮንጎ ተነጥሎ መታየት እንደሌለበት ያመለክታሉ። በሳቸው አመለካከት ብዙ የአፍሪቃ አገሮች ከፖለቲካ አንጻር ነፃ የወጡ ቢመስልም ራሳቸውን የቻሉ አይደሉም። ራሳቸውን እንዳይችሉ ደግሞ አሜሪካንና እንግሊዝ ልዩ ልዩ ሻጥሮችን እየሰሩ ወደ ርስ በርስ መበጣበጥ ያመሯቸዋል። በዚህ ዐይነት ኃላፊነት በጎደለው ፖለቲካ የአፍሪቃ ኤሊቶችና የአንግሎ-አሜሪካን አገዛዝ በመተባበር የአፍሪቃን ህዝብ ስቃይ እያራዘሙት ነው። በተለይም ቻይና እንደ አዲስ ኃይል ሆና ከወጣች ጀምሮ አፍሪቃን እንደገና ለመቀራመት የሚደረገው እሽቀድምድም ጦፏል። የነመለሰና የነሞሰቤኒና የነ ካጋሜ አጋጋዝ የአሜሬካንና የእንግሊዝ ውልዶች መሆናቸውን አቶ ፍሪዚከ ያመለክታሉ። ለብዙዎቻችንም ፣ ትግላችንን አጥብበን ለምንመለከት በሰፊውና በጥልቀት በመገንዘብ ከርስ በርስ ሽኩቻ ባሻገር ትግላችንን ባዲሰ መልክ እንድንቀይስ ይጋብዙናል። አቶ ፍሪዚከ እንደሚሉት አፍሪቃ ሁሉ ነገር አላት። ይህንን የተትረፈረፈ ሀብት የመጠቀም ጉዳይ የአፍሪቃ ህዝብ ሲሆን ፣ በአፍሪቃ ውስጥ እውነተኛ ዕድገት ሊመጣ የሚችለው የዓለም ኢኮኖሚ አወቃቀር ሲቀየርና ወደ ውስጥ ያተኮረ ዕድገት ሲቀየስ ብቻ ነው።

ቀጥለው የተናገሩት ከስዊድን የመጡ የሴት ተወካይ ሲሆኑ ፣ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያውያን ሴቶች ላይ የሚደረገው ጭቆና ከጊዜ ወደ ገዜ እየባሰ እንደመጣና ብዙ ወጣት ሴቶችም ወደ አረብ አገሮች በመሰደድ ፍዳን እንዲያዩ ተገደዋል።ይህ በዚህ መቀጠል እንደሌለበት በማስገንዘብ የኢትዮጵያን ሴቶች ነጻ ለማውጣት የሚደረገው ትግል እጥፍ ድርብ መሆን እንዳለበትና ይህም ትግል ከጠቅላላው የነጻነት ትግል ተነጥሎ መታየት እንደማይቻል አመልከትዋል። የወጣት ሴቶችና የወጣት ወንዶች ተጠሪዎች ንግግር በዚህ መንፈስ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ፣ የአገራችን ሀኔታ በዚህ መቀጠል እንደሌለበትና ትግላችንን በማስተባበር በንጹህ መንፈስ ወደ ፊት እንደንገፋና የታሪክም ኃላፊነት እንዳለብን አመልክተዋል።

ከዚህ በተረፈ የተፈጥሮ ሳይንስ ምሁርና በማይንዝ ዩንቨርሲቲ የሚሰሩት ዶክተር ጌዴዎን ጌታሁን ያቀረበት ንግግር ልዩ ቦታ የሚሰጠው ነው። ዶክተር ገዴዎን በአገራችን ስለ ደረሰው የአካባቢ መመረዝ ፣ የዛፍ መቆረጥና የመሬት መንሸርሸር ፣ እንዲሁም ኃላፊነት በጎደለው መልክ ሰለ ሚረጨው ማዳበሪያና የተባይ ማጥፊያ እጅግ አሳሳቢ እንደሆነ ጠቁመዋል። በተለይም በአገራችን ውስጥ እየተስፋፋ የመጣው የአበባ ተከላ ብዙ የእርሻ መሬቶችን እየተሻማ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን የማዳበሪያ አጠቃቀሙም ቅጥ ያጣ ከመሆኑ የተነሳ ወደ ፊት ልንወጣ የማንችለው ቀውስ ውስጥ እንደከተተን አሳስበዋል። በአገራችን የሚታየው የአካባቢ ቀውስም በዓለም አቀፍ ካለው ቀውስ ተነጥሎ መተያት እንደሌለበት በማመልከት ፣በአገራችን ግን ይህ የሚያሳስበው ኃይል እንደሌለና በዚህም ከከተማ ጽዳት ጀምሮ ህዝቡ ፣ መንግሰትና እንዲሁም የተማረው ኃይል አስተሳሰባቸውን በመቀየር በአዲስ መንፈስ በመነሳትና ዕድገትና የአካባቢ እንክብካቤ ተነጥለው መታየት እንደሌለባቸው ትምህርታዊ መልዕክት አስተላልፋዋል። ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ በአቀራረቡ ግሩም የሆነ ትምህርት የሁላችንም መመሪያ እንደሚሆንና ፣ አንድ ህዝብ በንጹህ አካባቢ ካልኖረ በበሽታ እንደሚሰቃይና ለመስራትም ሆነ ለማሰብ የግዴታ ቆንጆና በመርዝ ያልተበከለ የመኖሪያ ቦታ እንደሚያሰፈልገው አመልክተዋል።

የዕለቱን የመዝጊያ ንግግር ያደረጉት በጀርመን አገር የድሮ አምባሳድር የነበሩት የተከበሩ አቶ ዕምሩ ዘለቀ ናቸው። አቶ ዕምሩ ዘለቀ በወጣቱ ትውልድ ትከሻ ላይ ትልቅ የታሪክ ኃላፊነት እንደወደቀበት በማስገንዘብ ፣ አገራችንን ከጥፋት ለማዳን የሁሉም ፣ የባልቴቱም የሽማግሌውም ግዴታ እንደሆነ አባታዊ መልዕክታቸውንና ምክራቸውን

**አስተላልፈዋል። አምባሳደር ዕምሩ ለኢትዮጵያ ህዝብ ላላቸው የጸና ፍቅራና ለበጎ ስራቸው ከአዘጋጁ ሽልማት ተደርጎላቸዋል። ሌሎችም በቁም ነገርና በጸና ስራቸው የታወቁ ግለሰቦች እንደዚሁ በዚህ ዕለት ተሸልመዋል።**

**በተነጋታው ፣ እሁድ ዕለት ቤተክርሰቲያን ትልቅ ቅዳሴና ዝግጅት ተደርጎ ለሚሊኔዩሙ አከባበር ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል። ከአንድ ሺህ ኢትዮጵያዊ በላይ በተሰበሰበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥና ውጭ የተደረገው ጸሎትና ቅዳሴ ለብዞዎች የመንፈስ ጽናት እንደሰጠ የማይታበል ሀቅ ነው። እጅግ አስተዋይ በሆኑት ቄስ ልሳነ ወርቅ አማካይነት የተሰበሰበው ህዝብና በኋላም የታየው መስተንግዶና መዝሙሮች የሚያረጋግጠው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ለአገሩ ያለው ፍቅር የቱን ያህል እንደሆነ የሚያመለክት ነው። በተለይም በወጣት ሴቶችና ወንዶች የታየው የቤተ ክርስቲያን መዝሙር ዘመናዊ ከመሆኑም በላይ የሚያበረታታና በየቦታው ተበታትኖ ለሚኖሩት እህቶቻችንና ወንድሞቻችን አለኝታ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ወድ እህቶቻችን ከሺህ ህዝብ በላይ ለማስተናገድ እንጀራ ጋግረው ፣ ወጥ ሰርተው ፣ ጠላና ጠጅ ጠምቀው ማምጣቸው እጅግ የሚያስመሰግናቸው ነው። በፍራንክፈርት የታየው ይህ መሰባሰብ ፣ መተባበርና ለጋራ ዓላማ መነሳትና ለአገራችን ቆርጦ ለመታገል መሰባሰብና ድመጽን ማሰማት መቀጠል ያለበት ሲሆን ፣ በየቦታው የሚደረገው የማያስፈልግ የርስ በርስ ሽከኩቻም መቀጠል እንደሌለበት የሚያመለክት ነው። እንደተመለከትኩት ከሆነ አዲሱ ትውልድ ሽኩቻን አይፈልግም። የሚያስተምረውን እንጂ ተንኮልን አይሻም። ቀናን አመራር የሚፈልግና ለአገሩም ብልጽግና ለመታገል ቆርጦ የተነሳ ትውልድ ነው። በዚህ መንፈስ አዲሱ ዘመን የትብብር ፣ የሰላም ፣ የፍቅርና የብልጽግና እንዲሆን ለውድ አገራችን እንመኝላት። የዘመኑ የትግል መንፈስ ድህነትን ለማጥፋት ፣ ብልጽግናን ለማምጣትና የተከበረችና የተፈራች ኢትዮጵያን ለመገንባት የምንታገልበት መሆን አለበት።**

**አቀነባባሪ**
**ፈቃዱ በቀለ ከበርሊን**